# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

## የ2012 በጀት ዓመት ተጨማሪ በጀት አዋጅ

ቁጥር -----/2012 ዓ.ም

ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

ጥር 2012 ዓ/ም

## *አዋጅ ቁጥር -----/2012 ዓ.ም*

## *<u>የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ለ2012 በጀት ዓመት ለመደበኛና ለልማት ሥራዎች የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ፣</u>*

***መግቢያ፣***

*የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ወረዳዎች ከዕቅድ በላይ የሰበሰቡትን ገቢ አሳውጀው በሥራ ላይ ማዋል እንዲችሉ በተሻሻለዉ የክልሉ ህገ-መንገስት አንቀፅ 47/2/8 እና በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 95/2003 አንቀፅ 27 መሰረት ተጨማሪ በጀቱን ስራ ላይ ለማዋል ተጨማሪ በጀት ሆኖ በሚከተለዉ መልኩ ታዉጇል::*

***<u>አንቀፅ 1 ስያሜ</u>፣***

*ይህ አዋጅ ለ2012 በጀት ዓመት ለተጨማሪ ስራዎች የተፈቀደ በጀት አዋጅ ቁጥር -----/2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::*

***<u>አንቀፅ 2</u>: <u>የበጀት ዓመቱ ጊዜና የበጀት ምንጭ</u>***

*ከሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ የሚፈፀመዉ በአንድ በጀት ዓመት ጊዜ ዉስጥ ከማንዱራ ወረዳ፣ ከፓዊ ዶሮ ብዜትና ማሳደጊያ ማዕከል፣ ከፓዊ አጠቃላይ ሆስፒታል፣ ከፓዊ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ከአሶሳ ፖሊ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ፣ ከጣና በለስ ሴቶች አዳሪ ት/ቤት እና ከግልገል በለስ መምህራን ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ **ከእቅድ በላይ እና ከአሁን በፊት የተሰበሰበ ገቢ ብር 17,994,396.15** ፣ ከፓዊ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ **የተጣራ ሀብት ብር 145,131.82** እንዲሁም ከክልሉ ብዙዛን መገናኛ ድርጅት **ከሂሳብ መዝገብ ለሚሰረዝ የጥሬ ገንዘብ አልባ በጀት/Non Cash Budget/ ብር 50,755,325.61**፣ በተጨማሪም **ከፌድራል መንግስት ተጨማሪ ብድር ብር 150,000,000.00 በአጠቃላይ ድምር ብር 218,894,853.58 (ሁለት መቶ አስራ ስምንት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ስምንት መቶ አምሳ ሶስት ብር ከ58 ሳንቲም)** የተጨማሪ በጀት ሆኖ ስራ ላይ እንዲዉል በዚህ በጀት አዋጅ ተፈቅዷል::*

*ከመዝገብ የሚሰረዝ ሂሳብን በሚመለከት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 41/2003 አንቀጽ 39 እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት*

*የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም ክፍል 4 አንቀጽ 20 በተመለከተዉ መሠረት ሊሰበሰብ ያልቻለ ሂሳብ ከመዝገብ ለመሠረዝ/Right off/ በሚያዘዉ መሰረት የክልሉ መገናኛ ብዙሃን የ3 አዲስ FM ሬዲዮ ፕሮጀክት ማስፋፊያ ግንባታና መሳሪያዎች ግዥ ለፌድራል ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ በኩል ግዥዉ እንዲፈጸም ብር 64,227,292.76 ዉክልና ተሰጥቶ ከ2008 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ ጊዜ ለFM ሬዲዮ መሳሪያዎች ግዥ ለማከናወን ቅድመ ክፍያ ተከፍሎ የቆየ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ግዥ ተፈጽሞ ዕቃዎቹ ከቀረጥ ነፃ በመግባታቸዉ ብር 13,294,322.49 በ2009 በጀት ዓመት ተመላሽ ተደርጎ ለክልሉ ገ/ኢ/ል/ቢሮ ፈሰስ የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም ብር 170,978.66 በ2011 በጀት ዓመት በኤጀሲዉ በኩል ሳጋጠመዉ የጥሬ ገንዘብ እጥረት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ፈሰስ ሳይደረግ የተጠቀሙበት በመሆኑ በአጠቃላይ ግዥዉ በብር **50,755,325.61** ተፈፅሞ ቀሪ ብር 6,666 በፌዴራል ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ስም በተሰብሳቢ የተያዘ መሆኑ ተረጋግጧል። ስለሆነም በተሰብሳቢ የተያዘዉን ቀሪ ገንዘብ ተከታትለው እንዲያስመልሱ ሆኖ ብር **50,755,325.61** ማስረጃ የቀረበ ስለሆነ ሳይወራረድ በተሰብሳቢ የሚገኘዉን ሰነድ ጥሬ ገንዘብ የሌለዉ በጀት /Non Cash Budget/ በ2012 በጀት ዓመት ታውጆ በወጪ መመዝገብ እንዲቻል እና ሂሳቡ ከመዝገብ እንዲሰረዝ የክልሉ ም/ቤት ፈቅዷል።*

*<u>አንቀፅ 3</u>: <u>ተፈፃሚነት እና ኃላፊነት</u>*

*ተጨማሪ በጀት ሆኖ የተፈቀደላቸዉ የመንግስት መ/ቤቶች በመንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለመስሪያ ቤታቸዉ ሥራ ማከናወኛ ሲጠይቁ በ2012 በጀት ዓመት ተጨማሪ በጀት መሆኑ ታዉቆ የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እንዲከፍል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል::*

*አሻድሊ ሀሰን አልአጀብ*

*የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት*

*ፕሬዚዳንት*

*አሶሳ*

*ጥር 2012 ዓ.ም*

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ለ2012 የበጀት ዓመት ለመደበኛና ካፒታል በጀት በተጨማሪ ለታወጀዉ በጀት የወጪ አሸፋፈን**

## 1. ገቢ

### 1.1 ተጨማሪ የዉስጥ ገቢ

1.1.1. ማንዱራ ወረዳ……………………………………………………………790,270.46

1.1.2. የፓዌ ዶሮ ብዜትና ማሳደጊያ ማዕከል ከእቅድ በላይ የተሰበሰበ ገቢ……1,937,884.00

1.1.3. የፓዌ አጠቃላይ ሆስፒታል ከእቅድ በላይ የተሰበሰበ ገቢ…....................471,851.32

1.1.4. የፓዌ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከእቅድ በላይ የተሰበሰበ ገቢ..…………...…....710,827.00

1.1.5. የጣና በለስ ሴቶች አዳሪ ት/ቤት ተሰብስቦ ስራ ላይ ያልዋለ የዉስጥ ገቢ……….789,174.29

1.1.6. የአሶሳ ፖሊ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የዉስጥ ገቢ ………….1,969,423.59

1.1.7. የግልገል በለስ መምህራን ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ……...……………………..11,324,965.49

**ን/ድምር ……………………………..………………………………….17,994,396.15**

### 1.2 የተጣራ ሀብት

1.2.1. ፓዌ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ …………………..……………………………..145,131.82

**ን/ድምር ………………………………………………………………145,131.82**

### 1.3 ከመዝገብ ለሚሰረዝ ሂሳብ

1.3.1. የክልሉ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት...…..……………………………**50,755,325.61**

**ን/ድምር …….……………………………………..……………….. 50,755,325.61**

**1.4 ከፌዴራል መንግስት ተጨማሪ ብድር ……..…………………………...150,000,000.00**

**ጠቅላላ ገቢ ድምር ……..…………………..…………………..…………… 218,894,853.58**

## *2. <u>ወጪ</u>*

### *2.1 ለመደበኛና ካፒታል ወጪ*

- *ማንዱራ ወረዳ……………..……………………………………..…………790,270.46*
- *የፓዌ ዶሮ ብዜትና ማሳደጊያ ማዕከል …………………………………...1,937,884.00*
- *የጣና በለስ ሴቶች አዳሪ ት/ቤት ..............................................................789,174.29*
- *የፓዌ አጠቃላይ ሆስፒታል ………………………….......................471,851.32*
- *የፓዌ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ……………………………..........................855,958.82*
- *የአሶሳ ፖሊ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ…………………………..….1,969,423.59*
- *የግልገል በለስ መምህራን ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ…………………………...11,324,965.49*
- *የክልሉ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት...…..………………………...………..50,755,325.61*
- *የፌዴራል መንግስት ተጨማሪ ብድር ……..…..…………………...150,000,000.00*

***ጠቅላላ ወጪ ድምር…………………......…………………………….…..<u>218,894,853.58</u>***

## 3. በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ለ2012 በጀት ዓመት በተጨማሪ የታወጀ የመደበኛና ካፒታል ወጪ ዝርዝር

| ኮድ | የወረዳዉ/መ/ቤቱ ስም | መደበኛ | ካፒታል | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| **ጠቅላላ ድምር** | | **73,840,500.42** | **145,054,353.16** | **218,894,853.58** |
| 1. ከእቅድ በላይ የተሰበሰበ ገቢ እና የተጣራ ሀብት የታወጀ ን/ድምር | | 6,741,711.42 | 11,397,816.55 | 18,139,527.97 |
| 06/03/015 | ማንዱራ ወረዳ | 553,189.32 | 237,081.14 | 790,270.46 |
| 211/02/03 | የፓዌ ዶሮ ብዜትና ማሳደጊያ ማዕከል | 1,937,884.00 | | 1,937,884.00 |
| 311/02/03 | የጣና በለስ ሴቶች አዳሪ ት/ቤት | 157,834.86 | 631,339.43 | 789,174.29 |
| 311/05/02 | አሶሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ | 500,000.00 | 1,469,423.59 | 1,969,423.59 |
| 311/06/01 | የግልገል በለስ መምህራን ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ | 2,264,993.10 | 9,059,972.39 | 11,324,965.49 |
| 341/03/09 | የፓዌ አጠቃላይ ሆስፒታል | 471,851.32 | | 471,851.32 |
| 341/04/01 | የፓዌ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ | 855,958.82 | | 855,958.82 |
| 2. ከመዝገብ ለሚሰረዝ ሂሳብ የታወጀ ን/ድምር | | | 50,755,325.61 | 50,755,325.61 |
| 175 | የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት | | 50,755,325.61 | 50,755,325.61 |
| 175/03/01/00/002 | የF.M 91.4 ሬደዮ ጥናት፣ዲዛይንና ማስፋፊያ ፕሮጀክት | | 50,755,325.61 | 50,755,325.61 |
| 3. የፌዴራል መንግስት ተጨማሪ ብድር ን/ድምር | | 67,098,789.00 | 82,901,211.00 | 150,000,000.00 |
| 133 | ሠላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ | | 3,000,000.00 | 3,000,000.00 |
| 133/01/01/00/001 | የሚሊሻ አባላት አቅም ግንባታ ስልጠና | | 3,000,000.00 | 3,000,000.00 |
| 152 | የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ | **32,098,789.00** | **-** | **32,098,789.00** |
| 152/01/05 | የክልሉ ሀትመት | 2,700,000.00 | | 2,700,000.00 |
| 152/01/06 | የግብዓት ብድር ወለድ ክፍያ | 8,500,000.00 | | 8,500,000.00 |
| 152/01/07 | የፖሊስ ውዝፍ ደመወዝና የጡረታ ዕዳ ክፍያ | 20,898,789.00 | | 20,898,789.00 |

| ኮድ | የወረዳዉ/መ/ቤቱ ስም | መደበኛ | ካፒታል | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| **221** | **ውሃ፣መስኖና ኢነርጂ ሃብት ልማት ቢሮ** | | **4,000,000.00** | **4,000,000.00** |
| 221/01/01/00/047 | የቡለን ከተማ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት | - | 2,000,000.00 | 2,000,000.00 |
| 221/01/01/00/048 | የቱመት ሙከር የመጠጥ ውሃ መስመር ዝርጋታ | - | 2,000,000.00 | 2,000,000.00 |
| **273** | **የመንገዶች ግንባታና ጥገና ጽ/ቤት** | | **3,100,000.00** | **3,100,000.00** |
| 273/01/01/00/022 | የነባር መንገዶች ጥገና | | 3,100,000.00 | 3,100,000.00 |
| **274** | **መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ** | | **29,213,311.00** | **29,213,311.00** |
| 274/01/01/00/006 | ማንቡክ በለያ መንገድ ግንባታ | | 10,000,000.00 | 10,000,000.00 |
| 274/01/01/00/010 | የ3 መንገዶች ግንበታ ( ከያሶ-ሉጎበቃ፣ ቱመት-ጀበሮና-መኳር-አማኜ እና በልፉዲ- በዴሳ) | | 11,213,311.00 | 11,213,311.00 |
| 274/01/01/00/011 | የ3 መንገዶች ግንባታ (ዋና መንገድ - ድላሼ እና አባዲ፣ ሰኞ ገበያ- ገመድ እና ደብረዘይት-ሳንቂ - መልካን) | | 8,000,000.00 | 8,000,000.00 |
| **277** | **ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ** | | **15,000,000.00** | **15,000,000.00** |
| 277/01/01/00/003 | የክልል ም/ቤት እና የመስተዳድር ም/ቤት ህንፃ ግንባታ | | 15,000,000.00 | 15,000,000.00 |
| **311** | **ትምህርት ቢሮ** | | **5,000,000.00** | **5,000,000.00** |
| 311/01/01/00/005 | የመጽሐፍት ህትመትና የትምህርት ግብዓት ግዥ | | 2,000,000.00 | 2,000,000.00 |
| 311/05/01/00/002 | የድባጢ፣ የበሎጅጋንፎይ እና የሆሞሻ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ግንባታ | | 3,000,000.00 | 3,000,000.00 |
| **318** | **ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን** | | **3,000,000.00** | **3,000,000.00** |
| 318/01/01/00/001 | የአመራርና ባለሙያ የአቅም ግንባታ ስልጠና ፕሮግራም | | 3,000,000.00 | 3,000,000.00 |
| **341** | **ጤና ጥበቃ ቢሮ** | | **1,587,900.00** | **1,587,900.00** |
| 341/02/01/00/020 | በጤና ሚኒስተር የሚገነቡ የጤና ተቋማት ሻት ክፍያ | | 1,587,900.00 | 1,587,900.00 |
| **331** | **ስፖርት ኮሚሽን** | | **19,000,000.00** | **19,000,000.00** |
| 331/01/01/00/001 | አህመድ ናስር ሁለገብ ስታዲዮም ግንባታ /Phase III/ | | 19,000,000.00 | 19,000,000.00 |
| **462** | **መጠባበቂያ** | **35,000,000.00** | | **35,000,000.00** |
| 462/01/01 | መጠባበቂያ ለደመወዝና ሥራ ማስኬጃ | 35,000,000.00 | | 35,000,000.00 |